## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት

# ረቂቅ የኢነርጂ ፖሊሲ እና ማስፈጸሚያ ስልቶች

**የካቲት 2013**

**አዲስ አበባ**

ማውጫ


*1. መግቢያ................................................................................................ 0*

*2. የዘርፉ ራዕይ.............................................................................................. 1*

*3. የኢነርጂ ፖሊሲው መሻሻል አስፈላጊነት....................................................................... 1*

*4. ቁልፍ የፖሊሲ ጉዳዮች......................................................................................... 2*

*4.1. የኢነርጂ ድህነት መኖር (ዝቅተኛ የኢነርጂ አቅርቦት፣ ተደራሽነትና ኢፍትኃዊነት)........................................ 2*

*4.2. የአገልግሎት ጥራትና አስተማማኝነት ዝቅተኛ መሆኑ.............................................................. 2*

*4.3. በዘርፉ ጠንካራ ቁጥጥር/ሬጉላቶሪ ሥርዓት ያለመኖር......................................................... 3*

*4.4. ውጤታማ ያልሆነ የሃይል አጠቃቀም............................................................................ 3*

*4.5. የተዛባ ተቋማዊ የፋይናንስ አቋም.............................................................................. 3*

*4.6. የግል ባለሃብቶች በዘርፉ ውስጥ ያላቸው ሚና ዝቅተኛነት ............................................................ 3*

*4.7. ዘላቂ ያልሆነ የባዮማስ ሀብት አጠቃቀም....................................................................... 3*

*4.8. ዝቅተኛ ተቋማዊ ብቃትና የሰው ሀይል አቅም...................................................................... 4*

*4.9. ዝቅተኛ የቴክኖሎጂ ሽግግር አገራዊ ምርትና አገልግሎት ተጠቃሚነት........................................................ 4*

*4.10. የአካባቢና አየር ንብረት መዛባትና ለውጥ......................................................................... 4*

*4.11. የወጣቶች ተጠቃሚነት....................................................................................... 4*

*4.12. የአካል ጉዳተኞች እና ተጋላጭ የማህበረሰብ አካላት ከዘርፉ ልማት ፍትሃዊ ተጠቃሚነት................................ 4*

*4.13. ያልተጠናከረ ቀጠናዊና ዓለም አቀፍ ትብብር ........................................................................ 4*

*5. የፖሊሲው ዋና ግብ ....................................................................................... 4*

*6. የፖሊሲው ዓላማዎች....................................................................................... 5*

*7. የፖሊሲ ማስፈጸሚያ ስልቶች.................................................................................. 5*

*7.1. የኢነርጂ አቅርቦት........................................................................................ 5*

*7.2. የኢነርጂ አጠቃቀም........................................................................................ 9*

*7.2.1. የመኖሪያ ቤት ዘርፍ....................................................................................... 9*

*7.2.2. የትራንስፖርት ዘርፍ ....................................................................................... 9*

*7.2.3. የኢንዱስትሪ ዘርፍ........................................................................................ 10*

*7.2.4. የአገልግሎት ዘርፍ........................................................................................ 10*

*7.2.5. የግብርና ዘርፍ............................................................................................ 11*

*7.2.6. ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች......................................................................................... 11*

*8. የፖሊሲ አፈጻጸም ማዕቀፍ ... 14*
*8.1. የህግ ማዕቅፍ ... 14*
*8.1.1. ህጉ-መንግስት :- ... 14*
*የኢፌድሪ ህጉ መንግስት ስለልማት በግልጽ እንዳስቀመጠው ... 14*
*8.1.2. የኢነርጂ አዋጅ ... 15*
*8.1.3. የመንግስት እና ግል ኢጋርነት አዋጅ ቁጥር 1076/2010 ... 15*
*8.1.4. የአስፈጻሚ አካላትና ተቋማት አዋጆችና ደንቦች ... 15*
*8.1.5. የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ... 15*
*9. ፖሊሲውን የማስፈጸም ኃላፊነት ያለበት ተቋም ... 16*
*10. የፖሊሲ፤ የክትትል፣ የግምገማ እና የክለሳ ሥርዓት ... 17*
*11. የፖሊሲዉ ስርጭት ... 18*
*14.1. የኢነርጂ ጉዳዮች መረጃ አሰባሰብና ስርጭት ... 18*
*14.2. ኢነርጂ ጉዳዮች ግብረመልስ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ... 18*

# 1. መግቢያ

የኢነርጂው ዘርፍ በረጅም ጊዜ የዕድገት ጉዞው ሲታይ በሁሉም የሀገራችን የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ዘርፎች ላይ በሶስት መንገዶች ተፅዕኖዎችን ሲያሳርፍ ቆይቷል፡፡ **የመጀመሪያው** ኢትዮጵያ ነዳጅ አምራች ባለመሆኗ ወደ ሀገር ውስጥ ተገዝተው የሚገቡ የፔትሮሊየም ነዳጅ ውጤቶች አብዛኛውን የወጪ ንግድ ገቢን እየወሰዱ መገኘታቸው፤ **ሁለተኛው** ሀገሪቱ በፈጣን ሁኔታ እያካሄደች ያለችው የኃይል ዘርፉ ልማት ትልቁን የመንግሥት የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ድርሻ እየወሰደ መገኘቱ፤ እና **በሦስተኛ** ደረጃ ኢነርጂ በራሱ ለዘመናዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚ ግንባታ መሠረታዊ ግብዓት ወይም አስቻይ ሚናውን እየተጫወተ መሆኑ የሚጠቀሱ ናቸው።

ኢትዮጵያ ከወጪ ንግድ ከምታገኘው ገቢ አብዛኛውን የነዳጅ ውጤቶችን ለመግዛት እያዋለች በመሆኑ በውጭ ምንዛሪ ክምችት ላይ ጫና እያሣረፈ እንደሚገኝ ይታወቃል። የነዳጅ ዋጋ መዋዠቅ በሀገሪቱ ኢኮኖሚና የንግድ ሚዛን ላይ ስጋት ከማሳደሩም በላይ የኢነርጂ የአቅርቦት ደህንነት የማረጋገጥ ሂደት ላይ መዛባትን እየፈጠረ ስለሚገኝ ችግሩን በአጭርና በረጅም ጊዜ በሌላ አማራጭ መፍታት ይጠይቃል።

የሀገር ውስጥ አጠቃላይ የምርት መጠን ባለፉት 11 ዓመታት በአማካይ 10 ከመቶ በላይ ዕድገት ሲያዝመዘግብ የቆየ ሲሆን የህዝብ ዕድገቱም በአማካይ በየዓመቱ በ2.3 ከመቶ እያደገ ይገኛል። የሁለቱም ዕድገት በአንድ ላይ የኢነርጂ ፍላጐቱ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ አድርገውታል፡፡ በአጠቃላይ የዘመናዊ ኢነርጂ ዓይነቶች የሆኑት የኤሌክትሪክ ኃይል እና የነዳጅ ዘይት አቅርቦት ዕድገት እያሳዩ የመጡ ቢሆንም ከአጠቃላይ የኢነርጂ አጠቃቀም አንጻር ሲታዩ ድርሻቸው በጣም ትንሽ ነው ሲሆን በአንጻሩ የባህላዊ ባዮማስ ኢነርጂን ተጠቃሚ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል እጅግ ብዙ ነው፡፡ ይህ በመሆኑ በደን መራቆት እና በእናቶችና በህጻናት ጤንነት ላይ እያደረሰ ያለው ተጽዕኖ እጅግ አሳሳቢ ሆኖ የቀጠለ ጉዳይ በመሆኑ ሀገሪቱን በዓለም ካሉ ሀገራት **በኢነርጂ ድህነት** ዋነኛ ተጠቃሽ አድርጓታል።

የኢነርጂ ዘርፍ ልማቱን ከባህላዊ የባዮማስ ኢነርጂ ወደ ዘመናዊ የኢነርጂ አገልግሎቶች የሚደረገውን ሽግግር ለማፋጠንና መንግስት ያስቀመጠውን የአገር በቀል የኢኮኖሚክ ሪፎርም እንዲሁም የአስር ዓመት ዕቅድ ለማሳካት ከፍተኛ የሆነ የፋይናንስ ፍሰት ያስፈልጋል። እስካሁን ያለውን ሁኔታ ስንመለከት የኤሌክትሪክ ዘርፉን ለማልማት መንግሥት ከፍተኛውን የኢንቨስትመንት ድርሻ እየወሰደ ቢሆንም ዘርፉ ወጪውን የሚመልስ የታሪፍ ማስተካከያ ለረጅም ጊዜ ያልተደረገለት ስለነበር ለከፍተኛ የዕዳ ጫና የዳረገው ከመሆኑም በላይ የአገልግሎት አሰጣጡንም ደካማ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ መሆን ችሏል፡፡

በመሆኑም የግሉን ዘርፍ ማሳተፍ ወሳኝ እንደሆነ በመታመኑ በ2010 ዓም የወጣው የመንግሥትና ግል አጋርነት የሕግ ማዕቀፍ የግል ባለሃብቶች በኃይል ማመንጨትና ማከፋፈል ዘርፍ እንዲሳተፉ ሰፊ እድል ከፍቷል፡፡ ይህን ዕድል የበለጠ በማስፋት የግሉ ዘርፉ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲኖረው በኃይል ማመንጨት፤ የኃይል ማስተላለፍ እና ማሰራጨት ሥራዎች በተለያዩ ተቋማት እንዲከናወኑ ለማድረግ ተጨማሪ ሥራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

የአገራችን የኢነርጂ ምርት ከካርቦን ልቀት ነጻ በሆኑት በታዳሽ ኢነርጂ ምንጮች ላይ እንዲመሠረትና በቁጠባ ጥቅም ላይ እንዲውል የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ተግባራዊ እየተደረገ ባለው የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂ ውስጥ ዋነኛ ስትራቴጂ ሆኖ ተቀምጧል። ይህም እ.ኤ.አ በ2030 በተባበሩት መንግስታት የተቀመጠውን የምዕተ-ዓመቱ የልማት ግብ እና ዘላቂ የኢነርጂ ልማት ስትራቴጂ ጋር ተጣጥሞ እየሄደ ይገኛል፡፡

ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ያለው የኢነርጂ ፖሊሲ በታዳሽ ኢነርጂ ላይ ያተኮረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት በዓለማችንና በአገራችን በርካታ ለውጦች የተከሰቱ በመሆኑ ፖሊሲውን ማ`ሻሻል አስፈልጓል። ይህ እንዲሻሻል የተደረገው የኢነርጂ ፖሊሲም መንግስት ካስቀመጠው የሃገር በቀል ኢኮኖሚክ ሪፎርም፤ ከአስር ዓመቱ የልማት ዕቅድ ከአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂና የምዕተ-ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት የድርሻውን እንዲወጣ ታስቦ ተዘጋጅቷል። ከዚህም በተጨማሪ እንደ ሶላር ያሉ የታዳሽ ኢነርጂ ምንጮችን ለማምረት የሚረዱ አዋጭ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች በዋጋም በጥራትም በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ በመሆኑ አገራችንም ከኃይድሮ በተጨማሪ የኢነርጂ ቅልቅሉን ለማሳደግ በኢነርጂ ፖሊሲው ትኩረት እንዲሰጠው ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ የኢነርጂ ዘርፍ መሠረተ ልማት ከሌሎች የልማት ሥራዎች ቀድሞ በመገኘት ሌሎች የልማት ሥራዎችን በማነቃቃት ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ጉልህ አስተዋጾ ማበርከት ያለበት በመሆኑ ይህ እንዲሻሻል የተደረገው የኢነርጂ ፖሊሲ የኢነርጂ ሃብቶችን

በፍታህዊነት፤ በዘላቂነትና በአስተማምማኝነት በማልማትና አቅርቦትን በማሳለጥ የህብረተሰቡን ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እና የሃገር በቀል ኢኮኖሚክ ሪፎርሙን እና መዋቅራዊ ለውጡን በመደገፍ ፈጣን ሁለንተናዊ እድገት እንዲኖር በማስቻል ከኋላ-ቀር ኢነርጂ አጠቃቀም በመውጣት የኢነርጂ ድህነቱን ማስወገድ ይሆናል።

## 2. የዘርፉ ራዕይ

በ2022 ዓ.ም. ፍትሃዊ፣ ዘላቂ ፤ ተወዳዳሪ፤ ከብክለት የጸዳና፤ ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ዘመናዊ የኢነርጂ አቅርቦት የተረጋገጠባት ኢትዮጵያን ማየት ነው፡፡

## 3. የኢነርጂ ፖሊሲው መሻሻል አስፈላጊነት

ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ያለው የኢነርጂ ፖሊሲ በታዳሽ ኢነርጂ ላይ ያተኮረ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ሳይሻሻል ቆይቷል፡ ሆኖም በአሁኑ ወቅት በሀገራችንና በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተከሰተ ያለው የአየር ንብረት መዛባትና ለውጥ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለመቋቋም፤ በአገራችን ተግባራዊ እየሆኑ ያሉ መዋቅራዊና ትራንስፎርሜሽናል ለውጦች የሚጠይቁትን ከፍተኛ የኢነርጂ ፍላጐት በሚፈለገው ፍጥነት/ጊዜ፣ ዓይነትና ጥራት ብሎም በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ እንዲሁም በዘርፉ እየታዩ ያሉትን አዳዲስ የቴክኖሎጂ እምርታዎችን ለመጠቀም ሲባል ፖሊሲውን ማሻሻል አስፈልጓል፡፡

በዚሁ መሰረት የፖሊሲው መሻሻል አስፈላጊነት በሚከተሉት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ የተመሰረተ ነው፣

- የኢነርጂ ልማት ከሌሎች ልማቶች ቀድሞ በመገኘት ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ጉልህ አስተዋፀኦ ማበርከት የሚገባው ቢሆንም በሀገራችን እየተመዘገበ ያለውን ፈጣን የማክሮ ኢኮኖሚ እድገትን ተከትሎ በኢነርጂ ፍላጎት፤ አቅርቦትና ተደራሽነት መካከል ያለውን ልዩነት ማሻሻል የፖሊሲ ትኩረት የሚሻ በመሆኑ፣
- ሀገራችን እምቅ የታዳሽ ኃይል ምንጮች ባለቤት እንደመሆኗ መጠን ከዚህ ሀብቷ የራሷን የኢነርጂ ፍላጎት ከማሟላት ባሻገር ቀጠናዊ የኃይል ትስስሩን እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም የውጭ ምንዛሪ ምንጭን ለማሳደግ እንዲሁም ዘርፉ በአካባቢው ጂኦፖለቲካዊ መረጋጋት ላይ የሚኖረውን ሚና ከፍተኛ እንዲሆን ለማስቻል፣

- በአገር ደረጃ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እያስወጣ ያለውና ለአየር ንብረት ለውጥ መዛባት ምክንያት የሆነውን የፔትሮሊየም ነዳጅ በአሁኑ ወቅት ጥቅም ላይ እየዋሉ ባሉት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች (የኤሌክትሪክ ባቡር እና መኪና፣ በባዮፊዩል የሚንቀሳቀሱ መኪኖች፣ወዘተ ) መጠቀምና መተካት አስፈላጊ በመሆኑ፣
- በአሁኑ ጊዜ አዋጭ የሆኑ ከዋናው የኤሌክትሪክ ቋት እና ከቋቱ ዉጭ ያሉ ቴክኖሎጂዎች በስፋት ጥቅም ላይ በማዋል የዘርፉን አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል እና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆኑ በፖሊሲው ውስጥ እንዲካተቱ ለማድረግ፣
- በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል ሀገራት የፀደቀውን የ2030 (እኤአ) የዘላቂ የልማት አጀንዳ እና 17ቱን የዘላቂ ልማት ግቦች እንዲሁም የፓሪስ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ግቦችን ለማሳካት አስተማማኝ የኢነርጂ ልማት መኖር ወሳኝ በመሆኑ፡፡
- የኢነርጂ ምርትና ስርጭት ከብክለት የፀዳ እንዲሆን እንዲሁም በተጠቃሚው ወገን የኢነርጂ አጠቃቀም ብቃት እንዲሻሻልና የቁጠባ ባህል እንዲዳብር ለማድረግ፤
- የኢነርጂ ግብዓቶችን በሀገር ዉስጥ አቅም ለመፈብረክ፤ የሀገር በቀል ሀብት የገበያ ድርሻን ለማሳደግ፤ እንዲሁም የግል ባለሁብቶችን በዘርፉ መሪ ተዋናይ እንዲሆኑ ለማስቻል፤
- በሴቶች ላይ ከኋላ ቀር ኢነርጂ አጠቃቀምና አቅርቦት ጋር በተያያዘ ያሉባቸውን ችግሮች በማስወገድና ራሳቸውን እንዲያበቁ በማድረግ ለኢኮኖሚው እና ለራሳቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ፣
- የኢነርጂዉ ዘርፍ በራሱና ከሌሎች ዘርፎች ጋር በሚፈጥረው ጠንካራ መስተጋብር ለወጣቶች የተሻለ የሥራ ዕድልን ለመፍጠር አስፈላጊውን ዕገዛ ለማድረግ፤
- በኢነርጂ አሰራር እና አጠቃቀም የአካል ጉዳተኞች እና ተጋላጭ የማህበረሰብ አካላት ከዘርፉ ልማት ፍትሃዊ ተጠቃሚ መሆናቸዉን ለማረጋገጥ፤
- በኃይል ስብጥሩ ላይ የኒዉክለየር ኃይል ማመንጨትን እና ሌሎች አዋጪ የኢነርጂ ምንጮችን ለማካተት፤ ይህም የፖሊሲውን ትኩረት የሚሻ በመሆኑ፤ ናቸው፡፡

## 4. ቁልፍ የፖሊሲ ጉዳዮች

### 4.1. የኢነርጂ ድህነት መኖር (ዝቅተኛ የኢነርጂ አቅርቦት፣ ተደራሽነትና ኢፍትኃዊነት)

በሀገራችን አስተማማኝ፣ ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ፣ እንዲሁም የማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማትን በበቂ ሁኔታ የሚደግፍ የዘመናዊ ኢነርጂ አገልግሎት ባለመኖሩ ምክንያት በኢትዮጵያ ከፍተኛ የኢነርጂ ድህነት ይስተዋላል። ከአጠቃላይ የሀገሪቱ የኢነርጂ ፍጆታ እስካሁን የዘመናዊ ኢነርጂ ድርሻ እጅግ ትንሽ ነው፡፡ አሁን እየቀረበ ያለው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተደራሽነት ከ45 ከመቶ ያልዘለለ ከመሆኑም በላይ ኢፍትሃዊነት ያለበት ነው፡፡ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ የኤሌክትሪክ ፍጆታ ከ100 ኪሎ ዋት ሰዓት ያልበለጠ ሲሆን ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ካለው አማካይ (521 ኪሎ ዋት ሰዓት) ጋር ሲነፃፀር በብዙ ርቀት ወደ ኋላ ቀርቷል። ስለሆነም የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተደራሽነቱ እመርታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግና ፍትሃዊነቱን ማረጋገጥ የዘርፉ አንዱ ቁልፍ ጉዳይ መሆኑ፤

### 4.2. የአገልግሎት ጥራትና አስተማማኝነት ዝቅተኛ መሆኑ

የኃይል ማመንጨት በአብዛኛው በውሃ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ለአየር ንብረት መዛባት ተጋላጭ መሆኑ በተደጋጋሚ

ታይቷል፡፡ በተጨማሪም የማስተላለፊያ፣ማከፋፈያና ማሰራጫ ዘርፉ በበቂ ሁኔታ ያልተዳረሰ፤ የኃይል ፍላጎቱን በበቂ ሁኔታ መሸከም የማይችልና በየወቅቱ አስፈላጊ ጥገና የማይደረግለት ከመሆኑ ባሻገር ከፍተኛ የሆነ የፋይናንስና የአቅርቦት ውስንነት የሚታይበት ነው። ስለሆነም የዘመናዊ የኃይል ምንጭ ስብጥሩን በማስፋት፤ የማስተላለፊያና ማሰራጫ መሰረተ ልማትን በማጠናከርና የአሰራር ሥርዓቱን በማዘመን የዘርፉን የአገልግሎት ጥራትና አስተማማኝነትን ማረጋገጥ ስለሚገባ፤

### 4.3. በዘርፉ ጠንካራ ቁጥጥር/ሬጉላቶሪ ሥርዓት ያለመኖር

የኢነርጂ ደህንትንና ብቃትን እንዲሁም የጥራት ደረጃዎችን ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ የቁጥጥር/ሬጉላቶሪ ሥርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ የግሉ ዘርፍ፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት፣ ወዘተ በኢነርጂ ዘርፍ ልማትና ማሰራጨት ሥራ ላይ በስፋት እየገቡ ባለመሆኑ ግልጽ የሆኑ የአሰራር የህግ ማዕቀፍ የዋጋ ተመን ፖሊሲና የፋይናንስ አቅርቦት አሠራሮች ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉ፣

### 4.4. ውጤታማ ያልሆነ የሃይል አጠቃቀም

የኢነርጂ ማምረቻና መገልገያ መሣሪያዎች ብቃት ዝቅተኛና ኋላቀር በመሆኑ ለኢነርጂ ብክነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረጉ በመሆኑ ኢነርጂ ቆጣቢ በሆኑ አዲስ ቴክኖሎጂዎች መተካት አስፈላጊ በመሆኑ፤

### 4.5. የተዛባ ተቋማዊ የፋይናንስ አቋም

የኃይል አቅርቦት ዘርፉ ከወጪው አንፃር የተመጣጠነ ገቢ እያገኘ ባለመሆኑ የኦፐሬሽንና ጥገና ሥራውን በአግባቡ ማከናወን የሚያስችል የፋይናንስ ቁመና መፍጠር አልቻለም፡፡ ዘርፉ የመሠረተ ልማት ግንባታን በፋይናንስ የሚያደርገው ከራሱ ገቢ ብቻ ሳይሆን ከአገር ውስጥና ከአለም አቀፍ የአበዳሪ ተቋማት በሚገኝ ብድር በመሆኑ እና ይህንንም ብድር በአግባቡ ከገቢው መክፈል ባለመቻሉ ለተከማቸ ዕዳ ከመዳረጉ ባሻገር የተዛነፈ የፋይናንስ ሁኔታ እንዲፈጠር ምክንያት መሆኑ፤

### 4.6. የግል ባለሃብቶች በዘርፉ ውስጥ ያላቸው ሚና ዝቅተኛነት

ከባህላዊ የኢነርጂ አጠቃቀም ወደ ዘመናዊ የኢነርጂ አገልግሎቶች የሚደረገውን ሽግግር ለማፋጠን እና የመንግስትን የፋይናንስ ጫና ለመቀነስ በ2010 ዓ.ም የወጣው የመንግሥትና ግል አጋርነት የሕግ ማዕቀፍ የግል ባለሃብቶች በኢነርጂ ዘርፍ እንዲሳተፉ ሰፊ እድል የከፈተ በመሆኑ ይህን ዕድል የበለጠ በማስፋት የግሉ ዘርፉ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ምቹ ሁኔታን መፍጠር በማስፈለጉ፤

### 4.7. ዘላቂ ያልሆነ የባዮማስ ሀብት አጠቃቀም

የቤተሰብ ዘርፍ / መኖሪያ ቤቶች/ በኢትዮጵያ ትልቁ የኢነርጂ ተጠቃሚ ሲሆን ከጠቅላላው የኢነርጂ አቅርቦት ውስጥ 87 በሙቶ የሚሆነውን የሚጠቀም ዘርፍ ነው። በቤተሰብ ደረጃ ጥቅም ላይ ከሚውለው ኢነርጂ እስከ 92 በሙቶ የሚሆነው የባዮማስ ውጤት ሲሆን አጠቃቀሙም ከፍተኛ ብክነት የሚታይበት እና ለደን መራቆትና ለሴቶችና ህፃናት የጤና መታወክ አንዱ ምክንያት በመሆኑ የአጠቃቀም ብቃቱን ማሻሻል እና የዘመናዊ ኢነርጂ ተጠቃሚነትን ማሳደግ በማስፈለጉ፡

### 4.8. ዝቅተኛ ተቋማዊ ብቃትና የሰው ሀይል አቅም

በኢትዮጵያ የኢነርጂ ዘርፍ ውስጥ ከሚታዩት ዋነኛ ማነቆዎች አንዱ የሰው ኃይል አቅም ውስንነት፣ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ አሰራርና የፕሮጀክቶች የአስተዳደር ድክመት እንዲሁም ያልተረጋጋ ተቋማዊ አደረጃጀት የሚንፀባረቅበት በመሆኑ የዘርፉን ልማት ለማፋጠን በሥራ አመራር፣ በመዋዕለ ነዋይ ፍሠት፣ በቴክኖሎጂ፤ በዕውቀት እና በተቋማዊ አደረጃጀት ላይ ሁለንተናዊ ለውጥ ማምጣት በማስፈለጉ፤

### 4.9. ዝቅተኛ የቴክኖሎጂ ሽግግር አገራዊ ምርትና አገልግሎት ተጠቃሚነት

ሀገራችን ከወጪ ንግድ ከምታገኘው ገቢ አብዛኛዉን የምታውለው የነዳጅ ውጤቶችን ለመግዛት ነው። ይህ ሁኔታም በውጭ ምንዛሪ ክምችት ላይ ከፍተኛ ጫና እያሣደረ ሲሆን ዓለም አቀፍ የነዳጅ ዋጋ በጨመረ ቁጥር በኢኮኖሚውና ማህበራዊ ዘርፍ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ጫና ከፍተኛ እንደሆነ ታይቷል። በአጠቃላይ በኢነርጂ ዘርፉ ወጭ ቆጣቢ እና ፍትሃዊ አጠቃቀም ለማስፈን፤ በረጅም ጊዜ አማራጭ ሀገራዊ ምርት እንዲኖር ማድረግና በአጭር ጊዜ ነዳጅን በአማራጭ ቴክኖሎጂዎች የመተካትና በዘርፉ የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ በማስፈለጉ፤

### 4.10. የአካባቢና አየር ንብረት መዛባትና ለውጥ

በዓለም አቀፍ ደረጃ እየተከሰተ የሚገኘው የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ በኢነርጂው ዘርፍ ላይ የራሱ ተፅዕኖ እያሳረፈ በመሆኑ እና በውሃ ላይ በዋናነት ለተመሰረተው የአገራችን የኤሌክትሪክ የኃይል አቅርቦት ችግር ውስጥ እየከተተው በመገኘቱ ተጽዕኖውን ለመቋቋም የሚያስችል የአረንጓዴ ልማትን ስትራቴጂ በተቀናጀ መንገድ ለመተግበር በማስፈለጉ፣

### 4.11. የወጣቶች ተጠቃሚነት

የኢነርጂው ዘርፍ በራሱ እና ለሌሎች ዘርፎች በሚሰጠው አገልግሎት ለወጣቶች ስራ ፈጠራ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ትኩረት ሰጥቶ መስራት በማስፈለጉ፤

### 4.12. የአካል ጉዳተኞች እና ተጋላጭ የማህበረሰብ አካላት ከዘርፉ ልማት ፍትሃዊ ተጠቃሚነት

የኢነርጂ ዘርፉ በዚህ ረገድ ግልፅ የሆነ ፖሊሲ የሌለው በመሆኑ ትኩረት ሰጥቶ በፖሊሲው ማካተት በማስፈለጉ፤

### 4.13. ያልተጠናከረ ቀጠናዊና ዓለም አቀፍ ትብብር

ሀገራችን ካላት የታዳሽ ኢነርጂ ሃብት አንፃር ቀጠናዊ ትብብሩ በኤሌክትሪክ ዘርፉ በተወሰነ ደረጃ ያለ ቢሆንም የበለጠ ማጠናከርና በሌሎች ኢነርጂ ዘርፎችም ቀጠናዊ ትስስሩን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

## 5. የፖሊሲው ዋና ግብ

የፖሊሲው ዋና ግብ በፍታህዊነት፤ ዘላቂና አስተማምማኝ በሆነ አግባብ የሀገሪቱን የኢነርጂ ሃብት በማልማትና አቅርቦቱን በማሳለጥ የዜጎችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እንዲሁም የሃገር በቀል የኢኮኖሚክ ሪፎርሙንና መዋቅራዊ ለውጡን በመደገፍ በሀገሪቱ ፈጣንና ሁለንተናዊ ብልጽግና እንዲኖር ለማስቻል ነው።

## 6. የፖሊሲው ዓላማዎች

ከላይ የተጠቀሱትን ቁልፍ የፖሊሲ ጉዳዮችን ለመፍታት የኢነርጂ ፖሊሲው የሚከተሉትን ዋነኛ ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1. ተደራሽና ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው ዘመናዊ ኢነርጂ ለሁሉም ዘርፎች መቅረቡን ማረጋገጥ፣
2. የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን እንዲሁም የተለያዩ የታዳሽ ኢነርጂ ምንጮችን ስብጥር አዋጭ በሆነ አግባብ በማልማት የአቅርቦት ደህንነትና አስተማማኝነቱን ማሣደግ፤
3. የኢነርጂ ዘርፍ አስተዳደርንና የተቋም አቅም ግንባታን ማሻሻል፣
4. የኢነርጂ ዘርፉን የፋይናንስ ጤናማነት ማረጋገጥ፣
5. የግል ባለሃብቶች ተሳትፎን ማበረታታትና በዘርፉ በሚደረገው ኢንቨስትመንት የመሪነት ሚና እንዲኖራቸው ምቹ ሁኔታን መፍጠር፤
6. የኢነርጂ አቅርቦትና አጠቃቀምን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ደረጃ በማድረስ የኢነርጂ ድህነትን ማጥፋት፤
7. በኢነርጂ አቅርቦት የሂደት ሠንሠለትና ልማት ውስጥ የሴቶች ተጠቃሚነትን፣ ተሣታፊነትንና ውሣኔ ሠጪነትን ማሣደግ፣
8. የወጣቶችን፤ አካል ጉዳተኛ የሆኑና ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚነት በማስፋትና ሰፊ የስራ እድል እንዲፈጠር በማድረግ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ዘርፎች በሚገባ እንዲነቃቁ ማድረግ፤
9. የኢነርጂ አቅርቦትና አጠቃቀም የአካባቢያዊና ማህበራዊ ደህንነትንና ዘለቄታዊነትን የተከተለ መሆኑን ማረጋገጥ፣
10. ቀጠናዊ የሃይል ትስስርን በማበረታታት ታዳሽ ኢነርጂን በተወዳዳሪነት በማቅረብ የቀጠናውን ምጣኔ ሀብታዊ ውህድትን ማፋጠን፣

## 7. የፖሊሲ ማስፈጸሚያ ስልቶች

### 7.1. የኢነርጂ አቅርቦት

#### ሀ. የኤሌክትሪክ ዘርፍ

**ዓላማ - 1:** በዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ የኤሌክትሪክ ተደራሽነትን ማረጋገጥ፤

*የማስፈጸሚያ ስልቶች*

- ✓ የብሄራዊ የኤሌክትሪክ ቋት ሽፋንን በፍትሃዊነት በጥራትና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ የአጭር፤ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የልማት ዕቅድ ላይ በመመስረት የማልማት ስራን በቅንጅት መተግበር፤
- ✓ የኤሌክትሪክ አዉታሩን ልማት፤ አመራረቱንና አጠቃቀሙን ወጪ ቆጣቢ እንዲሆን በማድረግ የኤሊክትሪክ ዋጋን ተመጣጣኝ እንዲሆን ማድረግ፣
- ✓ የዜጎችን የመክፈል አቅም ያገናዘበ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ስርዓትና ደንብ መዘርጋት፣
- ✓ በኤሌክትሪክ ዘርፍ የአገር ውስጥ የግብዓት አምራቾችንና ኮንትራክተሮችን አቅም ከፍ ለማድረግ መደገፍ፣
- ✓ የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማትን ከሌሎች ሴክተር ልማት ፕሮግራሞች ጋር በቅንጅት መስራት፣
- ✓ ከብሄራዊ የኤሌክትሪክ ቋት ጋር ያልተያያዙ ታዳሽ የኃይል ምንጮችን ልማት እንዲስፋፋ ማድረግ፣

**ዓላማ - 2:** የኤሌክትሪክ አቅርቦት ጥራት፣ ደህንነትና አስተማማኝነቱን ማረጋገጥ፤

*የማስፈጸሚያ ስልቶች*

- ✓ ለውሃ ኃይል የተሰጠው ልዩ ትኩረት እንደተጠበቀ ሆኖ የኤሌክትሪክ አቅርቦቱን ይበልጥ አስተማማኝ ለማድረግ የሌሎች የታዳሽ ኃይል ምንጮችን በማልማት የኃይል ማመንጨት ስብጥርን ማሣደግ፣
- ✓ የኒውክሊየር ኢነርጂን ለኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫነት ለመጠቀም አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ እና ወደ ተግባር መግባት፣
- ✓ ኢንደስትሪዎች በተቀናጀ አሰራር የሃይል አቅርቦት እንዲያገኙ ለማድረግ የመሰረተልማትን በሰፊው መገንባት፣
- ✓ የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ ስርዓት መዘርጋት፣ ስታንዳርዶችና ኮዶችን ማዘጋጀት፣
- ✓ የኤሌክትሪክ ሃይል ብክነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ መመሪያዎችን ፤ ደንቦችንና የብቃት ደረጃዎችን ማዘጋጀትና መተግበር እንዲሁም አፈጻጸማቸውን መከታተል፤

**ዓላማ - 3:** የኤሌክትሪክ ዘርፍን የአስተዳደር እና የተቋማትን አቅም ማሻሻል፤

*የማስፈጸሚያ ስልቶች*

- ✓ በየደረጃው የቴክኒክ ዕውቀትና የአፈፃፀም ብቃት ያላቸው የባለሙያዎችን ለመፍጠር የታለመው የሥልጠና እና የአመራር ልማት መርሃግብሮች መተግበር
- ✓ በዘርፉ የአስተዳደር ነጻነት፤ ገለልተኝነት፤ግልጸኝነት፤ ተጠያቂነትና ብቃትን መሰረት ያደረግ የአሰራር ሥርዓት እንዲኖር የህግ ማዕቀፉን መከለስና ወቅታዊ ማድረግ፤
- ✓ የኤሌክትሪክ ዘርፉን የተሟላ መረጃ ስርአት በመገንባት ለሁሉም ባለድርሻ አካላት እንደየፍላጎታቸው ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ፤
- ✓ በኃይል ማመንጨት፣ ማስተላለፍና ማሰራጨት ዘርፍ ላይ የምርምርና ስርፀት ስራዎችን መደገፍ ፣
- ✓ የኤሌክትሪክ ስራ ተቋራጮች የብቃት ማረጋገጫ ስርዓት መዘርጋት፣ ስታንዳርዶችና ኮዶችን ማዘጋጀት፣
- ✓ የኤሌክትሪክ ሃይል ብክነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ መመሪያዎችን ፤ ደንቦችንና የብቃት ደረጃዎችን ማዘጋጀትና መተግበር እንዲሁም አፈጻጸማቸውን መከታተል፤
- ✓ የዘርፉን የተቋም ግንባታና የተቆጣጣሪ ባለስልጣኑን አቅም ማሳደግ፤

**ዓላማ - 4:** የኤሌክትሪክ ዘርፉን የፋይናንስ ጤናማንትን ማረጋገጥ፣

*የማስፈጸሚያ ስልቶች*

- ✓ የኤሌክትሪሲቲ ታሪፍን ከምክንያታዊ ወጭ ጋር ተመጣጣኝ በሆነና በግልጽ አሰራር እንዲመራ ማድረግ፣
- ✓ የመሰረተ ልማቶች ተገቢውን የአዋጭነት ጥናት መሰረት በማድረግ ግንባታቸው እንዲከናወን ማድረግ፤
- ✓ አዳዲስ ወጭ ቆጣቢ የሆኑ አሰራሮች እንዲተገበሩ ማድረግ፤
- ✓ የዘርፉን ተጓዳኝ ገቢ ማስገኛ ብቃት የሚጨምሩ ስራዎችን በመለየት በህግ ማዕቀፍ መደገፍና መተግበር፤
- ✓ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችንና የዘርፉን ዲጂታላይዜሽን የሚደግፍ የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ከቴክኖሎጂ መጠቀም

የሚያስኘውን ውጤታማነትን ማጎልበት፣

**ዓላማ - 5:** የግል ባለሃብቶችን፣ ማህበረሰቡንና የህብረት ስራ ማህበራትን በኤሌክትሪክ ዘርፍ ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ

***የማስፈጸሚያ ስልቶች***

- ✓ በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት፤ ማስተላለፍ፣ ማሰራጨት እና መሸጥ ስራዎች ላይ በየደረጃው ለሚሳተፉ የውጭና የአገር ውስጥ ባለሃብቶች አነቃቂ አዳዲስ ማበረታቻዎችን በጥናት በመለየት መተግበር፣
- ✓ ተወዳዳሪነትን የሚያበረታታ የኃይል ሽያጭና የአገልግሎት ታሪፍ ስርዓት መተግበር፣
- ✓ ማህበረሰቡን፣ የህብረት ስራ ማህበራትንና የሀገር ውስጥ የግል ባለሃብቱን በተለያዩ ስራዎች ላይ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ተዋናይ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀትና ብቃታቸውን ማጎልበት፤
- ✓ ለግል ፍጆታቸው ኃይል አመንጭተው የተረፋቸውን ለኃይል ቋቱ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚሸጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

**ዓላማ - 6 :** ቀጠናዊ የኤለክትሪክ ሃይል ንግድን ማጠናከር

***የማስፈጸሚያ ስልቶች***

- ✓ በቀጠናው ከሚገኙ አገራት ጋር የኃይል መሰረተ ልማት ትስስርን ማስፋፋት፣
- ✓ ቀጠናዊ የኃይል ግብይትን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የህግ ማዕቀፎች እንዲኖሩት ማድረግ፣
- ✓ ቀጠናዊ የኃይል ግብይትን የሚያጠናክሩ ትብብሮችን ማስፋት፣
- ✓ የምስራቅ አፍሪካ የሃይል ትስስር የተቋቋመበትን ዓላማ እንዲያስፈጽም ድጋፍ ማድረግ፡

## ለ. ባዮኢነርጂ ዘርፍ

**ዓላማ - 1: በዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ የባዮኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎች ተደራሽነትን ማረጋገጥ**

**የማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ✓ የባዮኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎችን በቅንጅት ማልማትና ተደራሽ ማድረግ፣
- ✓ የባዮኢነርጂ ቴክኖሎጂዎች በአዋጭነት ጥናት ላይ የተመሰረቱ ማድረግ፣
- ✓ ባዮፊዩል ለኢነርጂ አገልግሎት እንዲውል ማስፋፋት፣
- ✓ የባዮጋዝ ቴክኖሎጂን አጠቃቀምን ማሳደግና ተረፈ–ምርቱ ለማዳበሪያነት እንዲውል ማበረታታት፣
- ✓ የባዮኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎች ልማትን በጥናትና ምርምር ስራዎችን መደገፍ፣
- ✓ የባዮኢነርጂ ምንጮች ለኤሌክትሪክ ማመንጨት አገልግሎት እንዲውሉ ማበረታታት ፣

**ዓላማ - 2: የባዮኢነርጂ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ብቃት፣ ደህንነትና አስተማማኝነቱን ማረጋገጥ**

**የማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ✓ የማገዶ እንጨት አቅርቦት ዘለቄታዊ እንዲኖረው ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መስራት
- ✓ ተስማሚና ብቃት ያላቸው የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ማፍለቅ፤ ማሻሻል እና ማላመድ፣
- ✓ የተሻሻሉ የማብሰያ ቴክኖሎጂዎች የጥራት ደረጃ ማስጠበቅ፣
- ✓ ብክነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ስልቶችን፤ መመሪያዎችን ፤ ደንቦችን ማውጣትና መተግበር፣
- ✓ የቁጠባ ባህልን የሚያበረታቱ የሃይል ቆጣቢ መገልገያዎችን ለሚጠቀሙ ተጠቃሚዎች የተለየ ማበረታቻ እንዲኖር ማድረግ፤
- ✓ የቁጠባ ባህልን ለማጎልበት ለተጠቀቃሚዎች ትምህርትና ስልጠና መስጠት፣

**ዓላማ 3. ተቋማዊ አቅምን መገንባት፣**

**ማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ✓ ባዮኢነርጂን ለማስፋፋት ህግ ማዕቀፍ መከለስና ወቅታዊ ማድረግ፤
- ✓ የባዮኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎች የብቃት ማረጋገጫ ስርዓት መዘርጋት፣ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸው ስታንዳርዶችና ኮዶችን ማዘጋጀትና መተግበር፣
- ✓ የባዮኢነርጂ ቴክኖሎጂ የዕውቀት ማበልጸጊያ ማዕከላት እንዲሁም የሙከራና ሰርቶ ማሳያዎችን ማስፋፋት፣
- ✓ የባዮኢነርጂ ምንጭና ቴክኖሎጂ ልማት በትምህርት ካሪኩለም ለማካተት ከተለያዩ የምርምር ተቋማት፣ ዩኒቨርስቲዎች ጋር በቅንጅት መስራት፣
- ✓ የባዮኢነርጂ በገጠር ልማት ማስፋፊያ ፓኬጅ ውስጥ ማካተት፣

**ዓላማ - 4 : የግል ባለሃብቶች ያላቸውን ተሳትፎ ማሳደግ**

**የማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ✓ ለግል ባለሀብቱ ገበያ ተኮር የባዮኢነርጂ ልማት እንዲሳተፍ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣
- ✓ በየደረጃው ለሚሳተፉ የውጭና የአገር ውስጥ ባለሃብቶች አነቃቂ አዳዲስ ማበረታቻዎችን በጥናት በመለየት መተግበር፣

## ሐ. ሃይድሮ ካርቦን ዘርፍ

**አላማ - 1: የሃይድሮካርቦን ምርቶች አቅርቦትን ማረጋገጥ**

***የማስፈጸሚያ ስልቶች***

- ✓ በቂ ስትራቴጂያዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ አቅምን መፍጠር፣
- ✓ እንዳስፈላጊነቱ የነዳጅ ማጣሪያ በሀገር ውስጥ ማቋቋም፣
- ✓ የነዳጅ ማጠራቀሚያ፣ ማከማቻና የችርቻሮ ጣቢያዎች ብዛታቸውንና ስነምድራዊ ሥርጭታቸውን ሚዛናዊ

በሆነ መልኩ በግሉ ሴክተር ተሳትፎ እንዲስፋፋ ማድረግ፣

- ✓ በአገር ውስጥ የተፈጥሮ ጋዝ ለመጠቀም የሚያስል መሰረተ ልማቶችንና ቴክኖሎጂዎች መገንባት፣

**አላማ - 2:** ከውጭ በሚገቡ የነዳጅ ምርቶች ላይ ያለውን ጥገኝነት መቀነስ

***የማስፈጸሚያ ስልቶች***

- ✓ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚንቀሳቀሱ ተሸከርካሪዎች የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታ መዘርጋት ፣
- ✓ ባዮፊውል በዘርፉ ሊጫወት የሚችልውን ሚና በጥናትና ምርምር በመደግፍ ማሳደግ
- ✓ በባዮፊዩል የሚንቀሳቀሱ ተሽርካሪዎችን ማበረታታት ፣
- ✓ ለመብራትና ለማብስያ አገልግሎት እየዋለ ያለውን ኬሮሲን (ላምባን) በዘመናዊ በታዳሽ ኢነርጂ ምንጮች እንዲተካ ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መስራት፣

## 7.2. የኢነርጂ አጠቃቀም

### 7.2.1. የመኖሪያ ቤት ዘርፍ

**ዓላማ - 1 :- በዘርፉ የኢነርጂ አጠቃቀም ውጤታማና ኢነርጂ ቆጣቢ እንዲሆን ማድረግ፣**

**የማስፈጻሚያ ስልቶች**

- ✓ የተሻሻሉ የኢነርጂ ቆጣቢ መገልገያ ቴክኖሎጂዎች እንዲለሙ ማበረታታትና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማስተዋወቅ፣
- ✓ እንደ የዋጋ ተመን አሠራር ፣ የግብር እፎይታ በመሳሰሉ አሰራሮች አማካኝነት የፀሐይ ሙቀት አማቂ ቴክኖሎጂን በስፋት ማስተዋወቅ
- ✓ የተሻሻሉና ኢነርጂ ቆጣቢ መገልገያ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ ፣
- ✓ ዘመናዊ ታዳሽ የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምን የሚያበረታታ ስርአትን መዘርጋት፣
- ✓ በተሻሻሉ የኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች ላይ የሚደረግ ጥናት፣ ምርምር እና ስርጸትን መደገፍ፣
- ✓ በኢነርጂ ብቃት እና ቁጠባ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ፣

### 7.2.2. የትራንስፖርት ዘርፍ

**ዓላማ :- የዘርፉ የኢነርጂ አጠቃቀም ውጤታማና ኢነርጂ ቆጣቢ እንዲሆን ማድረግ**

**የማስፈጻሚያ ስልቶች**

- ✓ ከፔትሮሊየም ውጭ የሆነን የኢነርጂ አማራጮችን የሚጠቀሙ የትራንስፖርት የቴክኖሎጂዎችን ማበረታታት፣
- ✓ ሞተር አልባ የትራንስፖርት አማራጭን ማበረታታት፣
- ✓ ፣
- ✓ የኢነርጂ ቆጣቢ የትራንስፖርት ቴክኖሎጂዎችን በሃገር በቀል አምራቾች እንዲገጣጠሙና እንዲመረቱ ማበረታታት፣

- ✓ የኤሌክትሪክ ተሽርካሪዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማበረታቻዎችን ማመቻቸት፣
- ✓ የኢነርጂ አጠቃቀማቸዉ ውጤታም ያልሆኑ ተሽከርካሪዎችን ደረጃ በደረጃ ከመንገድ ማስወጣትና ነዳጅ ቆጣቢዎችን ማበረታታት፣
- ✓ ኢነርጂ ቆጣቢ የሆኑ የመንገድ አውታሮች፤ የከተማ ልማትና የትራፊክ ፍሰት እንዲቀላጠፍ የተቀናጀ አሰራር እንዲኖር ማድረግ፣
- ✓ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ በዘርፉ ውስጥ ያሉትን ባለድርሻ አካላት ግንዛቤን ማሳደግ፣

### 7.2.3.የኢንዱስትሪ ዘርፍ

**ዓላማ :-**

1 **የኢንዱስትሪዎች ኢነርጂ አጠቃቀም ውጤታማና ኢነርጂ ቆጣቢ እንዲሆን ማድረግ፣**

**የማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ✓ ኢነርጂ ቆጣቢ አሰራሮችንና ቴክኖሎጂዎችን ማበረታታትና መደገፍ፣
- ✓ ኢነርጂ አባካኝ የሆኑ ማሽነሪዎችን ከስራ ውጭ እንዲሆኑ የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፣
- ✓ እንደ የዋጋ ተመን አሠራር ፣ የግብር እፎይታ በመሳሰሉ አሰራሮች አማካኝነት የፀሐይ ሙቀት አማቂ ቴክኖሎጂን በስፋት እንዲጠቀሙ ማድረግ
- ✓ ኢንደስትሪዎች የሚፈልጉትን የሃይል መጠን በራሳቸው እንዲያመነጩ ማበረታታት፣
- ✓ የኢነርጂ ኦዲት ደንብ ማውጣት ፣ የኢነርጂ ኦዲት ተቋማት እንዲፈጠሩ ማገዝ ፤ አቅም መገንባት እና ወቅታዊ የኃይል አጠቃቀም ኦዲት በተገቢው ጊዜ እንዲሰራ ማድረግ፣
- ✓ የተሻሻሉና ኢነርጂ ቆጣቢ መገልገያ ቴክኖሎጂዎችን ኢንዱስትሪዎች እንዲጠቀሙ የሚያስገድዱ የህግ ማዕቀፎችንና የብቃት ደረጃዎችን ማዘጋጀት፣

### 7.2.4.የአገልግሎት ዘርፍ

**ዓላማ :- የዘርፉ የኢነርጂ አጠቃቀም ውጤታማና ኢነርጂ ቆጣቢ እንዲሆን ማድረግ**

**ማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ✓ በኢነርጂ ብቃትና ቁጠባ በዘርፉ ውስጥ ያሉትን ባለድርሻ አካላት ግንዛቤን ማሳደግ፣
- ✓ የተሻሻሉና ኢነርጂ ቆጣቢ መገልገያ ቁሶችን በአገልግሎቱ ዘርፍ ውስጥ በጥቅም ላይ እንዲውሉ ማበረታታት፣
- ✓ እንደ የዋጋ ተመን አሠራር ፣ የግብር እፎይታ በመሳሰሉ አሰራሮች አማካኝነት የፀሐይ ሙቀት አማቂ ቴክኖሎጂን እንዲጠቀሙ ማበረታታት
- ✓ የተሻሻሉና ኢነርጂ ቆጣቢ መገልገያ ቁሶችን በአገልግሎቱ ዘርፍ ውስጥ መጠቀምን የሚያስገድዱ የህግ ማዕቀፎችንና የብቃት ደረጃዎችን ማዘጋጀት፣
- ✓ አገልግሎት ሰጪዎች ታዳሽ የኤሌክትሪክ አማራጮችን እንዲጠቀሙ ማበረታታት፣
- ✓ ኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም የሚያስችል የፋይናንስ ማበረታቻ ስርአትን መተግበር፣

**7.2.5.** የግብርና ዘርፍ

ዓላማ ፡-

1. **የዘርፉ የኢነርጂ አጠቃቀም ውጤታማና ኢነርጂ ቆጣቢ እንዲሆን ማድረግ፣**

**ማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ✓ አማራጭ ኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ለግብርናው ዘርፍ በሚውል መልኩ ማልማትና ማስፋፋት፣
- ✓ ከፍተኛ መስኖ ልማቶች የሚፈልጉትን የሃይል መጠን በራሳቸው እንዲያመነጩ ማበረታታት፣
- ✓ ኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ለግብርና ባለሙያዎች፤ አርብቶ አደሩንና አርሶ አደሩን ማስተዋወቅና ስልጠና መስጠት፣
- ✓ አርብቶ አደሩንና አርሶ አደሩን የግብርና ተረፈ ምርቶችን ለራስ ፍጆታ በዘመናዊ ኢነርጂ ማመንጨት እንዲጠቀሙ ማብቃትና ማበረታታት
- ✓ ኢነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም የሚያስችል የፋይናንስ ማበረታቻ ስርአትን መተግበር

**7.2.6.** ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች

**ሀ. የሴቶች ጉዳይ**

**ዓላማ ፡-** በኢነርጂ ልማትና አስተዳደር እንዲሁም አገልግሎት የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግና የስርዓተ ፆታ ፍትሃዊነትን ማረጋገጥ፣

**የማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ✓ የዘመናዊና ታዳሽ የኢነርጂ ምንጮችንና ቴክኖሎጂዎችን በማልማት ሂደት የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የማበረታቻ ስርአት መዘርጋት፣
- ✓ የስርአተ ጾታ ስብጥርን የሚያሳይ የመረጃ አያያዝ፤ ግምገማና የተስተካከለ የተሳትፎ ምጣኔ እንዲኖር የሚረዳ ግልጽ አሰራርን መዘርጋት፣
- ✓ በኢነርጂ ዘርፍ ላይ የሴቶችን የትምህርት ዝግጅትና ስልጠና በማሳደግ በኢነርጂ ዘርፉ ወደ ውሳኔ ሰጪነት እንዲመጡ ለማድረግ የሚረዱ አስራሮችን ማበረታታት፣
- ✓ ሴቶች የዘመናዊ የኢነርጂ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም የሚያስችላቸውን የፋይናንስ አቅርቦት በተለየ ሁኔታ ማመቻቸት

**ለ. የአካል ጉዳተኞች እና ሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች**

**ዓላማ ፡-** የአካል ጉዳተኞች እና ሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በኢነርጂ ልማትና አስተዳደር ስራዎች ላይ ያላቸውን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ

**የማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ✓ የአካል ጉዳተኞች እና ሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በኢነርጂ ዘርፉ ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ አግባብ ያላቸው ቴክኖሎጂዎች እና የአሰራር ሂድቶች ጥቅም ላይ ማዋል፣
- ✓ የዘመናዊና ታዳሽ የኢነርጂ ምንጮችን በማልማት ስራ ላይ የአካል ጉዳተኞች ሌሎች ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ እንዲጨምር ማበረታቻ ስርአት መዘርጋት፣

**ሐ. የወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት**

ዓላማ ፡- ወጣቶች በኢነርጂ ልማትና አስተዳደር ስራዎች እና በሌሎች ዘርፎች ላይ ያላቸውን ሚና እና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣

**የማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ✓ የዘመናዊና ታዳሽ የኢነርጂ ምንጮችን በማልማት ስራ ላይ የወጣቶች ተሳትፎ እንዲጨምር ማበረታታት፣
- ✓ የቴክኖሎጂ ፈጣሪ የሆኑ ወጣቶች በጥናት ፣ ምርምር እና ስርጸት ሥራ ላይ ተሳትፏቸዉን ማሳደግና የፋይናንስ አቅርቦቱን ማመቻቸት
- ✓ ለወጣቶች ስራ ፈጠራና የስራ ዕድል ለሚያመቻቹ አካላት የኢነርጂ አቅርቦት በአስተማማኝ ሁኔታ ማድረስ፣

**መ. የአካባቢና ማህበራዊ ዘርፍ**

አላማ፡- የአካባቢያዊና ማህበራዊ ደህንነትንና ዘለቄታዊነትን ያረጋገጠ የኢነርጂ ልማትን ዕውን ማድረግ

**የማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ✓ የአካባቢያዊና ማህበራዊ ደህነንትን ለማስጠበቅ የወጡ ህጎችና ደንቦችን በዘለቂያታዊነት ማስጠበቅና የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ
- ✓ የአካባቢን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀንስ ታዳሽ ባልሆኑ ቴከኖሎጂዎች ላይ የአካባቢ ጉዳት ግብርን መጣል
- ✓ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለውና በየጊዜው በሚሻሻል መልኩ የደህንነት ኮዶች መቅረጽና እንዲተገበር ማድረግ
- ✓ የሃይል ማመንጫ ግድቦችን በደለል እንዳይሞሉ ተገቢውን የተፋሰስ ልማትን መደገፍ፣
- ✓ ለታዳሽ ሃይል ግንባታ የሚያበረታቱ አሰራሮችን መቅረጽና መተግበር፣
- ✓ ኢነርጂን ለምርታማነት ፣ ለገቢ ማስገኛና ለስራ ፈጠራ እንዲውል ማበረታታት፣

**ረ. የኢነርጂ ዘርፍ የፋይናንስ ድጋፍ**

**I. የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ**

ዓላማ፡-

1. ለኢነርጂ መሠረተ ልማትና አስተዳደር በቂ ፋይናንስ እንዲኖር ማድረግ፣
2. የፋይናንስን ውጤታማነትና ቀልጣፋ አጠቃቀምን ማረጋገጥ፣

**ማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ✓ ለኢነርጂ ዘርፍ ኢንቨስትመንት አዋጪ ጥናትና ፕሮፖዛሎችን በጥራት ለማቅረብ የሚያስችል አቅም መገንባት፣
- ✓ የኢነርጂ ዘርፍ የኢንቨስትመንት ዕቅዶችን ከአጠቃላይ ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ የልማት እቅዶች ጋር ማጣጣም፣
- ✓ አማራጭ እና አዳዲስ የመንግሥት ፋይናንስ ዘዴዎችን ማበረታታት፣
- ✓ በዘርፉ ያለውን የፋይናንስ አስተዳደር አቅምን ማጠናከር፣
- ✓ የገጠር ኢነርጂ ማስፋፊያ ፈንድን ለማስተዳደር ደንብና መመሪያን ማዘጋጀትና መተግበር፣
- ✓ የኢነርጂ ፈንድ ተዘዋዋሪ ገንዘብ እና የረጅም ጊዜ የባለ ዝቅተኛ ወለድ ብድር ተደራሽነትን ማመቻቸት፣

**II. የማህበረሰብ የፋይናንስ ድጋፍ**

ዓላማ ፡- የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማሳደግ ለኢነርጂ ልማት፣ አቅርቦት እና አስተዳደር ሥራዎች የሚውል ሀብት ማሰባሰብና መጠቀም፣

**ማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ✓ የማህበረሰብ አደረጃጀቶች፣ የህብረት ስራ ማህበራት የኢነርጂ ልማት ፋይናንስ ውስጥ በንቃት እንዲሳተፉ ማድረግ፣
- ✓ በማህበረሰብ ደረጃ ለሚሰሩ የኢነርጂ ልማትና አስተዳደር ስራዎች አነስተኛ ብድር ተደራሽነትን ማሳደግ፣

**III. የልማት አጋሮች እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የፋይናንስ ድጋፍ**

አላማ:-

1. ከልማት አጋሮች እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለኢነርጂ ልማትና አስተዳደር የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍ ማሰባሰብና ጥቅም ላይ መጠቀም ፣
2. ከልማት አጋሮች እና የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች የሚገኝ የገንዘብ እና ሌላ ሀብትን በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን በማጎበረቡ ፣ በፌዴራል እና በክልል ኤጀንሲዎች በቅንጅት መፈጸሙን ማረጋገጥ፣

**ማስፈጸሚያ ስልቶች**

- ✓ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮችን እና የፋይናንስ ፍላጎቶችን ግልፅ በማድረግ ለዘርፉ የሀብት ማሰባሰብ ስትራቴጂ ማዘጋጀት::
- ✓ ለልማት አጋሮች እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አማራጭ የፋይናንስ አቅርቦት መንገዶችን ማዘጋጀት፣
- ✓ በመደበኛነት የኢነርጂው ዘርፍ ፋይናንስ ሁኔታ መረጃን በአግባቡ ለልማት አጋሮች እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በግልጽ ማቅረብ፣
- ✓ የኢነርጂ ተቋማትን ከልማት አጋሮች የሚገኝ ገንዘብን አያያዝ እና አጠቃቀም አቅምን ማጎልበት:
- ✓ ከልማት አጋሮች እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለኢነርጂ ሀብት ልማት እና አስተዳደር የሚገኘውን የገንዘብ

ድጋፍ ለህዝብ ማሳወቅ እንዲሁም ሪፖርቶችን ማውጣት፣

- ✓ በፌዴራል እና በክልሎች የዘርፉ ተቋማት እንዲሁም በልማት አጋሮች እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች መካከል የትብብር ስርዓቶች እንዲኖሩ ማበረታታት፣

### IV. የግሉ ዘርፍ የፋይናንስ ድጋፍ

ዓላማ ፡ ለኢነርጂ ሀብት ልማትና አቅርቦት የግሉ ዘርፍ ፋይናንስን ማጎልበት፣

ማስፈጸሚያ ስልቶች

- ✓ የግሉ ዘርፍ በኢነርጂ ልማትና አስተዳደር ላይ መዋዕለ-ንዋይ እንዲያፈስ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
- ✓ ተገቢ ህጎች ደንቦችን እና ተቋማትን በመመስረት የሀገር ውስጥ ፋይናንስ አቅምን (የአገር ውስጥ ካፒታል ገበያ) መጠቀም እንዲቻል ማድረግ
- ✓ የመንግስት እና የግል አጋርነትን በማጎልበት የግሉን ዘርፍ የቴክኒክ እና የአስተዳደር ብቃትን እንዲሁም ፣ የፋይናንስ ድጋፍ ለኢነርጂ ዘርፍ ልማት፣ አቅርቦት እና ተያያዥ አገልገሎቶች ላይ መጠቀም፣
- ✓ አዳዲስ የፋይናንስ ሞዴሎችን መፈለግ እና መተግበር፣
- ✓ የግሉ ዘርፍ በተለይ አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች ከብሄራዊ የኃይል ቋት ውጪ በኢነርጂ ልማትና አስተዳደር ላይ እንዲሳተፉ መደገፋ እና ማበረታታት፣
- ✓ በኢነርጂ ሀብት ልማት፣ አቅርቦትና አስተዳደር ላይ የግሉ ዘርፍ ማህበራዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ማበረታታት፣

## 8. የፖሊሲ አፈጻጸም ማዕቀፍ

የኢነርጂ ዘርፍ ፖሊሲ አፈጻጸም ማዕቀፍ ሀገራዊ እምቅ የኢነርጂ ሃብትን በአጭር፤ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ በማልማት እና ፍላጎትን ስኬታማ በሆነ መልኩ ለማርካት የሚያስችል አቅጣጫ ለመጠቆም የተዘጋጀ ነው፡፡ በዘርፉ የሚሳተፉ ሁሉም ባለድርሻ አካላትም ሚናና ሃላፊነታቸው በግልጽ ተለይቶ እንዲታወቅና ወጥነት ያለው አፈጻጸም እንዲኖር ያስችላል፡፡ የፖሊሲ ማስፈጸሚያ ማዕቀፉ ሁሉንም አገራዊ የኢነርጂ ምንጮች በፍትሃዊነት ለማልማት፣ ለማስተዳደርና ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ አዋጆች፤ መመሪያዎችና ኮዶችን ለማዘጋጀት እንደ መነሻ ሆኖ የሚያገለግል ይሆናል፡፡

### 8.1. የህግ ማዕቅፍ

#### 8.1.1. ህገ-መንግስት :-

**የኢፌድሪ ህገ-መንግስት ስለልማት በግልጽ እንዳስቀመጠው**

- ✓ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአጠቃላይም ሆነ በኢትዮጵያ ያሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች በተናጠል የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡
- ✓ ዜጐች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማኅበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሐሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡
- ✓ መንግሥት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚገባቸው ስምምነቶችም ሆኑ የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች የኢትዮጵያን

የማያቋርጥ እድገት ሙብት የሚያስከብሩ መሆን አለባቸው፡፡

- ✓ የልማት እንቅስቀሴ ዋና ዓላማ የዜጐችን እድገትና መሰረታዊ ፍላጐቶች ማሟላት ይሆናል፡፡

ይህ ፖሊሲም የኢፌድሪን ህገ-መንግስትን መሰረት አድርጓል።

**8.1.2.የኢነርጂ አዋጅ:**

ለኢነርጂ ልማትና አስተዳደር በተገቢው መልኩ መመራት ይቻል ዘንድ የሚከተሉት አዋጆችና ደንቦችን ታሳቢ ተደርጓል፥-

- ✓ የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006
- ✓ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 308/2006
- ✓ የኢነርጂ (ማሻሻያ) አዋጅ 1085/2011
- ✓ የጂኦተርማል ሀብት ልማት አዋጅ ቁጥር 981/2008
- ✓ የጂኦተርማል ሀብት ልማት የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ 453/2011
- ✓ የኢነርጂ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 447/2011
- ✓ የኢንቨስትመንት አዋጅ 1080/2012
- ✓ የኢንቨስትመንት ደንብ 474/2012

**8.1.3.የመንግስት እና ግል አጋርነት አዋጅ ቁጥር 1076/2010**

- ✓ በኢነርጂው ዘርፍ ውስጥ የግል ባለሃብቱን ተሳታፊነትና የመሪነት ሚናን ለማረጋገጥ የመግአን አዋጅን እንደ መነሻ ተውስዷል።

**8.1.4.የአስፈጻሚ አካላትና ተቋማት አዋጆችና ደንቦች**

**8.1.5.የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ**

- o የኢነርጂ ዘርፉን ማልማትና ማስዳደር
- o የኢነርጂ ዘርፉን ማስተባበር
- o ፋይናንስ ማፈላለግና የብድር አቅርቦት
- o ፍትሐዊነት እና አካታችነት ማረጋገጥ
- o የኢነርጂ ፕሮግራም/ፕሮጀክት አመራር
- o ሌሎች. . .

## 9. የፖሊሲው ተፈፃሚነት ወሰን

የዚህ ፖሊሲ ተፈጻሚነት በአገራዊ የኢነርጂ ጥናቶች ፣ እቅዶች (አጭር፤ መካከለኛንና ረጅም) ፣ ልማቶችና የአስተዳደር ስራዎች ላይ ይሆናል፡፡ የፖሊሲው ተፈጻሚነት ከዚህ በታች በተገለጹት ዘርፎች ላይ ያተኩራል፡-

- ✓ የኤሌክትሪክ ዘርፍ፣
- ✓ የነዳጅ ዘርፍ፣
- ✓ የባዮ ኢነርጂ ዘርፍ፣
- ✓ የኢነርጂ አጠቃቀም ብቃትና ቁጠባ፣
- ✓ ከኢነርጂ ጋር የተገናኙ የዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን ያካተተ ነው

## 10.ፖሊሲውን የማስፈጸም ኃላፊነት ያለበት ተቋም

ይህንን የኢነርጂ ፖሊሲ በዋናነት የማስፈጸም ሃላፊነት ያለበት የውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሲሆን አጠቅላይ ተቋማዊ መዋቅርም ከዚህ በታች እንደተመለከተው ነው፡-

I. **የውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር፤**
   - የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ሃላፊነት ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1097/2011፤

II. **የገንዘብ ሚኒስቴር**
   - የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ሃላፊነት ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1097/2011፤
   - የመግአ አዋጅ ቁጥር 1076/2010

III. **የመአድንና ነዳጅ ሚኒስቴር**
   - የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ሃላፊነት ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1097/2011፤

IV. **የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን፤**
   - የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር 810/2006
   - የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 308/2006
   - የኢነርጂ (ማሻሻያ) አዋጅ 1085/2011
   - የጂኦተርማል ሀብት ልማት አዋጅ ቁጥር 981/2008
   - የኢነርጂ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 447/2011
   - የጂኦተርማል ሀብት ልማት የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ 453/2011
   - የኢንቨስትመንት አዋጅ 1080/2012
   - የኢንቨስትመንት ደንብ 474/2012

V. **የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል፡**
   - የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 302/2006

**VI. የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፤**

- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 302/2006

**VII. የገጠር ኢነርጂ ልማት ማስፋፊያ ማዕከል፤**

- የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ሃላፊነት ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 1097/2011፤

**VIII. የግል አልሚዎች**

- የመግአ አዋጅ ቁጥር 1076/2010

## **11.** የባለድርሻ አካላትና ሚናቸው

**የዚህ የኢነርጂ ፖሊሲ ዋና ዋና ባለድርሻ አካላትና ሚናቸው ከዚህ በታች እንደተገለጸው ነው።**

- ✓ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ ዐዋጆችን በማውጣት፤ ዕቅድና ክንውን በመከታተል፤
- ✓ የፌዴሬሽን ምክር ቤት፤ የፍታሃዊነት የልማት ቀመርን በማውጣትና ክንውን መከታተል፤
- ✓ የሚኒስትሮች ምክር ቤት፡ ደንቦችንና ፖሊሶዎችን በማውጣት፤ ዕቅድና ክንውን በመከታተል፤
- ✓ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች፤ የኢነርጂ የልማት ስራዎችን የመደገፍና በባለቤትነት የድርሻቸውን መወጣት፤
- ✓ የሴክተር መስሪያቤቶች፤ የተቀናጀ የልማት እቅድ በመንደፍና ስኬታም የትገበራ ስራን መወጣት፤
- ✓ የልማት አጋሮች፤በኢነርጂ ልማትና አስተዳደር ስራዎች ድጋፍና ትብብር ማድረግ፤
- ✓ የግል አልሚዎች፤በኢነርጂ ልማት በግል እንዲሁም ከመንግስት ጋር በሽርክና መገንባትና ማስተዳደር፤
- ✓ አበዳሪ ተቋምት፤ለኢነርጂ ዘርፉ የፋይናንስ አቅርቦት ማመቻቸት፤
- ✓ ዜጎች፤በዘመናዊ መልኩ የለሙ የኢነርጂ አቅርቦትን በቁጠባ በመጠቀም ሃገራዊ የፖሊሲ ግቦችን ማሳካት፤

## **12.**የፖሊሲ፤ የክትትል፣ የግምገማ እና የክለሳ ሥርዓት

የውሃ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር የፖሊሲውን ተግባራዊነት እና ውጤታማነት የሚለኩ የአፈጻጸም አመላካቾን በመለየት በየተወሰነ የጊዜ ርቀት ይከታተል ይገመግማል፡፡ ለአስፈፃሚ ዘርፎች የማስፈጸሚያ ስልቶች በማዘጋጀት አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል። ፖሊሲውን ከሚያስፈፅሙ ሌሎች ተቕማት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

ይህንን ፖሊሲ ለመተግበር ሁሉንም ባለድርሻ አካላት አቀናጅቶ መሥራት ይጠይቃል። በዘርፉ የተቀናጀ አስተዳደርን የሚያጎለብቱ አደረጃጀቶችና አሠራሮች ይዘረጋሉ። የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና የክልል የኢነርጂ ቢሮዎች ወይም ዘርፉን እንዲያስተዳድሩ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የጋራ የምክክር መድረክ በማጠናከር የፖሊሲ፣ የማስፈጸሚያ ስልትና ዕቅድ በማዘጋጀት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ይፈጸማሉ።

በፌደራል፣ ክልል፣ ዞንና ወረዳ ደረጃ ከዘርፉ ልማት አጋሮች ጋር የምክክር መድረክ በማጠናከር የሀገራችን የኢነርጂ ሀብት ልማት ፖሊሲ፣ የማስፈጸሚያ ስልት፣ የሕግ ማዕቀፍ እንዲሁም በየደረጃው የሚዘጋጁት ዕቅዶችና መመሪያዎች ተግባራዊ እንዲሆኑ

ይደረጋል።

ለፖሊሲው ተግባራዊነት በዘርፉ የቁጥጥር ሥርዓትን ለማቋቋም የሚያስችለውን ማዕቀፍ ለመዘርጋት አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ተዋናይ ባለድርሻ አካላትን ማሳተፍ ያስፈልጋል። ስለሆነም የፖሊሲውን አፈፃፀምና በዘርፉ የሚገኘውን የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነት ለማረጋገጥ እና በሚታዩ ድክመቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ በየደረጃው የክትትልና ግምገማ ሥርዓቶች ተዘጋጅተው ይተገበራሉ።

በአጠቃላይ ፖሊሲውንና የማስፈጸሚያ ስልቶቹን ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ አደረጃጀቶች እንደየአስፈላጊነቱ በማዋቀር የሚጠበቀውን ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት ይደረጋል። ስለዚህም በፌደራል ደረጃ የኢነርጂ ሴክተርን የሚመራው ሚኒስቴር መ/ቤት የፖሊሲውን አፈጻጸም በመከታተላልና በመገምገም ቁልፍ ሚና የሚጫወት ይሆናል። ፖሊሲው ቢያንስ በየ 5 ዓመቱ እየገመገመ እንዲሻሻል ያደርጋል።

## 13.የፖሊሲዉ ስርጭት

### 13.1. የኢነርጂ ጉዳዮች መረጃ አሰባሰብና ስርጭት

የኢነርጂ ተጠቃሚዎች እና የሌሎች ባለድርሻ አካላትን ፍላጎት ያማከለ የኢነርጂ ሃብት፣ የኢነርጂ አቅርቦትና ፍጆታና ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎች አሰባሰብና ስርጭት ዘመናዊነትና ተደራሽ በሆኑ የሃገር ውስጥና የዓለም አቀፍ ቁንቋዎች አንዲሰበሰብና እንዲሰራጭ ማደረግ።

- ✓ የኢነርጂ መረጃ በተሟላ መልኩ በመሰብሰብ፣በማከማቸትና በማቀነባበር ለሞዴሊግ፣ ለፖሊሲና፣ ስትራቴጂዎች እንዲሁም ለሌሎች የኢነርጂ ሃብት ልማት ዕቅዶች ዝግጅት ግብአት እንዲሆን የመረጃ ባንክና ሥርዓት መገንባት፤
- ✓ የኢነርጂ ሃብት፣ አቅርቦትና ጥቅም ላይ ስለዋለው የኢነርጂ መጠን እንዲሁም ስለ ወደፊት የኢነርጂ ፍላጎት ሁሉን አቀፍና አስተማማኝ ትንበያን ያካተተ የተቀናጀ የኢነርጂ ሀብትና ልማት ወቅታዊ መረጃ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ይሆናል፤
- ✓ የሴክተሩን መደበኛ አፈጻጸም በየወቅቱ አመቺና ዘመናዊ የመረጃ ማሰራጪያዎች በመጠቀም ለሁሉም አካላት እንዲደርስ ይደራጋል፤
- ✓ በየወቅቱም የተለያዩ መድረኮችና የስልጠና ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት የኢነርጂ ዘርፉን የሚመለከቱ ውይይቶችና የአቅም ግንባታ ስራዎች ይሰራሉ፤

### 13.2. ኢነርጂ ጉዳዮች ግብረመልስ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

- ✓ በየወቅቱም የተለያዩ መድረኮችና ውይይቶችን በማዘጋጀት ግብረመልስን ማግኘት፤
- ✓ በዘመናዊ የግብረመልስ መሰብሰቢይ አማርጮችን በመጠቀም የባለድርሻ አካልትና የኢነርጂ ተጠቃሚዎችን የእርካታ ደረጃ፤ ተጨማሪ ፍላጎቶቸና አስተያየቶችን መሰብሰብ፤

## የቃላት ፍቺ

1. **ኢነርጂ** :- አንድን ነገር የሚያንቀሳቅስ ወይም ሙቀትና ብርሃን የሚሰጥ ኃይል ሲሆን የሚገኘውም ከማገዶ፣ከድንጋይ ከሰል፣ ከነዳጅ ዘይት፣ ከኤሌክትሪክ፣ ከጸሃይ፣ ከእንፋሎትና ከሌሎች እንዲሁም ከሰውና ከእንስሳት ጉልበት ነው፡፡ በዚህ ፖሊሲ ውስጥም በዋናነት የኤሌክትሪክ (ከተላያዩ የሃይል ምንጮች የሚገኘውን) ፤ የሃይድሮ ካርቦን ፤ የባዮ ፊውልና ከኒዩክለር የሚገኝን የሃይል ልማትን፤አቅርቦትንና አጠቃቀምን ይመለከታል።
2. **ታዳሽ ኢነርጂ፡-** ከፀሐይ ብርሃን ፣ ከነፋስ ፣ ከውሃ ፣ ከእንፋሎትና ከመሳሰሉት ከካርቦን ነጻ ከሆኑ ምንጮች ጨምሮ የሚገኝ ኃይል ነው ፡፡
3. **የባዮማስ ኢነርጂ** :- ባዮማስ ኤሌክትሪክ ወይም ሙቀት ለማመንጨት እንደ ነዳጅ ወይም ግብዓት የሚያገለግል ከእጽዋት ወይም ከእንስሳት ተረፈ ምርት ወይም ቅሪት የሚገኝ ቁስ ነው፡፡
4. **ሃይድሮፓወር** :- የውሃን ጉልበት በተለያየ አቅምና ደረጃ በመጠቀም የኤሌክትሪክ ኃይልን ማመንጨት ነው፡፡
5. **ጂኦተርማል ኢነርጂ፡-** በማንኛውም ሁኔታ ከመሬት ገጸ-ምድር በታች የሚገኝ ሆኖ ከተፈጥሯዊ የመሬት ሙቀት የተገኘ ወይም የተፈጠረ ወይም ከዚሁ የተፈጥሮ ሙቀት ውስጥ የወጣ ኢነርጂ ነው
6. ሶላር **ኢነርጂ : -** የፀሐይ ሙቀትና እና ብርሃን በመጠቀም የሚገኝ ታዳሽ ኃይል ነው ፡፡
7. **ባዮ ኢነርጂ** :- ባዮኢነርጂ ለማገዶ ጥቅም ላይ የሚውሉትን ልዩ ልዩ ዛፎችና ሰብሎች ጨምሮ የሰዎች፤ የእፅዋትና የእንሰሶች ቆሻሻን የሚያጠቃልል ሲሆን በአግባቡ ከተያዘ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ትልቅ ኃብት ነው፡፡
8. **ሃይድሮካርቦን፡-** ከቅሪተ አካል የሚገኝ ነዳጅ ነው፡፡
9. **ባዮፊዩል -** በካርቦ ሃይድሬት እና በዘይት ከበለጸጉ የተክሎች ግንድ፣ ፍሬ፣ ስር ወይም ቅጠል፤ የከተማ ውጋጅ፣ የግብርናና የደን ተረፈ ምርት፣ አልጌ፣ ወይም የእንሥሳት ስብ እና ጥቅም ላይ ከዋለ ዘይት በማቀነባበር የሚገኝ ታዳሽ የሆነ ፈሳሽ ነዳጅ ማለት ነው፤
10. **የኢነርጂ አቅርቦት አስተዳደር** :- ኢነርጂን ከማልማት ጀምሮ እስከ ተጠቃሚው የማድረስ ሂደት በብቃት ከብክነትና ከብክለት በጸዳ መልኩ መከናወኑን ለማረጋገጥ የሚከናወኑ እርምጃዎችን ያመለክታል ፡፡
11. **የኢነርጂ አጠቃቀም አስተዳደር :-** የኢነርጂ ተጠቃሚ አካላት የኢነርጂ ፍጆታቸው ከብክነትና ከብክለት ነጻ በሆነ አግባብ እንዲሆን በፍላጎትና በአስገዳጅ ደንቦች የሚተገበሯቸው እርምጃዎችን የሚገልጽ ነው፡፡

12. **የምስራቅ አፍሪካ የሃይል ትስስር ተቋም**፡- ኢትዮጵያን ጨምሮ በ11 የምስራቅ አፍሪካ ሃገራት በትብብር የኤሌክትሪክ ንግድን እርስ በርስ በተቀናጀ መልኩ በመተሳሰር ለማቀላጠፍ የተመሰረተ ተቋም ነው።
13. **የኑክሌር ሃይል ፡-** ኒውክለርን በማብላላት የሚፈጠረውን ሙቀት በዋናነት ውሃን በማፍላት የሚፈጠረውን እንፋሎት ለኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫነት ማዋልን ይመለከታል።
14. **የኢነርጂ ብቃት፡-** በዝቅተኛ የኢነርጂ ፍጆታ ተመሳሳይ ወይም ከፍ ያለ ምርት ወይም አገልግሎት ማቅረብ መቻል ነው፡፡
15. **የኢነርጂ ቁጠባ፡-** በአንድ ሂደት ወይም ስርዓት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውለውን የኢነርጂ መጠን ብክነትን በማስወገድ እና ኢኮኖሚያዊና አግባብ በሆነ አጠቃቀም መቀነስ ነው፡፡
16. **የኢነርጂ ደህንነት፡-** ለአንድ ሃገር እያደገ የሚሄደውን የሃይል ፍላጎት መሸከም የሚችል አስተማማኝ የኢነርጂ ልማትን፤ አቅርቦትንና አጠቃቀምን ታሳቢ ያደረገ ሃሳብን ይመለከታል።
17. **ባዮጋዝ -** ከእስሳትና ከእጽዋት የሚገኝ ተረፈ ምርትን በመፍጨትና በማብላላት የሚፈጠር የጋዝ ነዳጅ ነው፡፡
18. **የብሄራዊ የኤሌክትሪክ ቋት -** አገራዊ የኃይል አቅርቦትን በዋናነት የሚሸከም ከተያያዙት ኃይል ማመንጫዎች ወደ ተጠቃሚዎች ኃይል የሚዳረስበት የተማከለ መረብ (ግሪድ) ነው፡፡